**Koongireesii Uummata Oromoo**

# OROMO NATIONAL CONGRESS

# የኦሮሞ በሔራዊ ኮንግረስ

## የኦሮም በሄራዊ ኮንግረስ ማን ነው ምንድን ነው።

የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ እዲቋቋም ምክንያት ከሆኑ ዋናዋና ሁኔታዎች መካከል ሊታሰብ የሚገባው ቁምነገር ዘመናዊው የኦሮሞ ህዝብ በሔራዊ ስሜት ከዘመናት እንግልት በኋላ በ1950ዋቹ አመታት ማቆጥቆጡ ነው፥ በዙሃኑ የኦሮሞ ህዝብ በኢትዮጵያ መንግሥት በሲቪልና በወታደራዊ ቢሮክራሲ ውስጥ ሲሳተፉ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ ይፈጸም የነበረ የበታች አድርጎ የመቁጠር ባህሪን ለመለወጥና በኢትዮጵያ ብዙ ቁጥር ያለው የ ኦሮሞ ህዝብ ይህን ገዢ በነበረውው ሥርዓት ላይ ተቃውሞና አገር አቀፍ ቅሰቀሳ በማድረግ ሲንቀሳቀስ ቆይቶአል። ከታሪክ እደምንረዳው ለዘመናት የኦሮሞ ህዝቦች በልዩ ልዩ መልክ ገዢውን ሥርዓት ሲታገሉና ሲያታገሉ ተዘግበዋል ለምሳሌ ያህል በጀነራል ዋቆ ግቱ ይመረ የነበረው የባሌ ኦሮሞ እንቅስቃሴ አንዱ ሲሆን በልማት ሰምም የተደራጀው የመጨናቱለማ የመረዳጃ ማህበርም ተጠቃሽ መሆን ይችላል  በመሰረቱ ብዙ የትግል የባህልና የልማት ታሪክ ያለው የኦሮሞ ህዝብ በ1960ዎቹ በኢትዮጵያ የተስራፋውን ባልባታዊ ሥር ዓት ለመታገል ሁሉንም ህዝብ በማስተባበርና በማሳታፊ በኦሮሞ ተወላጆች አመራርና በብዛት ተሳታፊነት የ አጼውን አስተዳደር በመቃወም ትግል ተጀመረ በምህጻረ ቃላት መኢሶን የሚባለው በኦሮሞ ህዝብ በሄራዊ ሰሜት የተካነ ቡድን መላው የኢትዮጵያ ህዝበን በማነቃነቅ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄን ታሪክ ማንም የሚዘነጋው አይሆንም ምንም እንኳን የኦሮሞ ተወላጆች በብዛት በ አመራርና በበዛት በዚህ ነቅናቄ ቢሳተፉም በዚህ ተጻራሪ ነት የኦሮሞ ህዝበ ለብቻው መነግሥት ማቋቋም አለበት በሚል ኦነግ የተበለ ድርጅት በ1966 በአበዮቱ ሰዓት በመመሥረቱ ሰፊውን የኦሮሞ ህዝበ በማቀፍ የተቀሰቀሰው ንቅናቄ ግቡን እዳይመታ ታልቅ አስተዋጾ በማድረግ የመሰመር ልዩነትና መከፋፈልን ፈጥሮ እስከዛሬ ድረስ የኦሮሞ ህዝብ ትግልን ግብ አርቆታል። ለዚህ ነው የኦሮሞ በሄራዊ ኮንግረስ በሚል ስም ተደራጅተን ትግላችንን በአገር ውስጥና በውጭ እይታገለን ያለ ነው።

ከላይ የተዘረዘረውን አስመልክተን በአሁን ሰዓት በስልጣን ላይ ያለው መንግሥትም ነጻነትን ዲሞክራሲንና እኩልነትን አመጣለሁ ቢልም ከዚህ ውጭ በጉልበት ና ፍትሃዊ ባለሆነ ሂደት ሥልጣን ላይ ቁጭ በሎ አሁንም በኦሮሞ ህዝቦች ላይ በራሱና በፈጠረው አሻንጉሊት በኦፐዲዮ ብሎ በሰየመው ቡድን አፍንህ ግዛ የሚል መርሁን ተጋባራዊ እያደረገ ነው፥፤ ኦብኮ* የኦሮም በሄራዊ ኮንግረስ* ይህን የማናለብኝነት ሥርዓት  በተገኘው አማራጭና ቀዳዳ እየታገለ ይገኛል የኢህአዴግ መንግሥት በድርጅታቸን ስም ተቀጥላ ቢፈጥርምና አባሎቻችን ውስጥ ሰርጎ ገብ ፈጥሮ ሊከፋፈለን ቢሞክርም በሰፊው አባሎቻንና በሰፊው ደጋፊዋቻቸን ብርታት ትግላችንን በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ እያቀጣጠል ነው እንገኛለን፥ ባሳለፍነው የዘጠኝ ዓመት የትግል ጉዞ በዙ ውጣውረድ መከራን እሥርና ሁነኛ ደጋፊዎቻችንና አበባሎቻችንም የህይወት መሰዋትነት ጠይቆአል፥፤
ዛሬ የ ኦሮሞ ህዝብ በ አንድነት በ እኩልነት የሰፊው ህዝብ ባህል ቋንቋና ነጻነት ተከበሮ በምንም ነገር

ምራጫው ተከብሮለተ ተቻ ተሎ ለመኖር የሚያደረገው ትግል ወደፊት እየታራመደ ይገኛል ።ለዚህ ምሥክር እስከዛሬ ያላየነውን እውነታ በኢትዮጵያ በተካሄደው ምርጫ 97 በተሳተፍነበት ቦቱ ሁሉ የኦሮም በሄራዊ ኮንግረስ ተመራጩች አሸነፈናል በ እኛ ስም በድርጅታችን ስም ለምርጫ የተወዳደሩ አድርባዮች ሳይቀር የህዝበብ ድምጽ ሊያገኙ ችለዋል ያም ዛሬ የድርጅታችንን ህልውናን በመሸፈጥ እንቅስቃሴ ቢያደርጉም በገዢው መንግሥት ሃይል ጋር ተባብረው ቢያነገላቱንም ምሥክራቸን የሆነውን የኦሮሞን ህዝብ ይዘን አጋሮቻችንን ለነጻነት የሚታገሉ ሁሉን በማስተባበር በውስጥም በውጭም ትግላችንን እያቀጣጠልን ነው። ዛሬ ልዩነቶቻችንን በማቻቻል ጠቃሚና ዘላቂ ለሆነው የህዝባችን ነጻነት

በዓለም አቀፍ ደረጃ ትግላችንን በማስታወዋቅ ነጻነት የጠማው ወገን ሁሉ ከጎናችን ሆኖ ለማየት ችለናል ህዝባችንም በዚህ ሰዓት በትንንቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን ወደኋላ እደማይመለስ ከምናቀርበቻው መረጃዎች ሃቅን ማየት ይችላል;፡

የኦሮሞ ህዝብ ያሸንፋል።

## የኦሮም በሄራዊ ኮንግረስ ዓላማዎች;

1- የኦሮሞ ህዝብ የራሱን ዕድል የመወሰን መብቱ የራሱ የህዝቡ በመሆኑ እንዲከበር
2- የኦሮሞ ህዝብ በሄራዊ መብቱ ተጥብቆለት በሄርዊ ሃብቱንም በተሻለ መንገድ እዲቆጣጠር የመንግሥቱም ቅርጽ ፌድራላዊ ዲሞክራሲያዊ እዲሆን
3- የኦሮሞ ህዝብ በሄራዊ ሃብቱ ያለምንም ተጽኖ እዲውልና በትግል የተቀዳጀው የመሬት ላራሹ አዋጅ መሰረታዊ ይዘት ሳይቀየር ለኢኮኖሚ ጠቀሜታ ባለው መልኩ ተግባራዊ እዲሆን።
4- የኦሮሞ ህዝብ ቋንቋ ተስፋፍቶ በየደርጃው ትምህርትም እንዲሰጥበት በኢትዮጵያ አብዛኛው ህዝብ የሚናገረው ቋንቋ ስለሆነ የብሄራዊ ቋንቋ እንዲሆን
5- የኦሮሞ ህዝብ በ እኩልነት ባህሉ ታሪኩና ሥፍራው ተከብሮለት ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ጋር በዲሞክራሲያዊነት ተስማምቶ እዲኖር ነው፥

በዚህ ላይም የኦሮሞ ህዝብ የከፋፍለህ ግዛ ሴራ ሰለባ ሳይሆን ከሌሎች ህዝቦች ጋር ሆኖ ሁሉንም በ እኩልነት ለሚያስተናግድ ደሞክራሲያዊ ስርአት በሚደረገው ትግል ተገቢ ሚና መጫወት ነው።

**info@ oromonc.org**

Bank Acc/No. Oromo National Congress
Awash Bank S, C.
Arat Kilo Branch
Acc/No. 266
Code: Awinetaa